
# የACPS Express 8/19/2022: የእንኳን ደህና-መጣችሁ መልዕክት፣ ከዶ/ር ሚላኒ ኬ-ዋየት (Dr. Melanie Kay-Wyatt)

## የእንኳን ደህና-መጣችሁ መልዕክት፣ ከዶ/ር ሚላኒ ኬ-ዋየት (Dr. Melanie Kay-Wyatt)



በአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) ውስጥ፤ ሁሉም ተማሪዎች - በኦገስት (Aug.) 22 ቀን ለመመለስ-በተዘጋጁበት-ጊዜ፤ የ2022-23 የቀለም-ትምህርት ዓመት መጀመሩ-ነው። ከሴፕቴምበር (Sept.) 1 ቀን 2022 ጀምሮ፣ እንደ ጊዜያዊ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጅ ሆነው የሚያገለግሉት፤ የACPS፣ የሰው-ኃይል አስተዳደር (Human Resources) ዋና-ሹም - ዶ/ር ሚላኒ ኬ-ዋየት (Dr. Melanie Kay-Wyatt)፤ ለአዲሱ የትምህርት ዓመት፣ አንዳንድ-የመቀበያ ቃላቶችን አጋርተዋል። በተጨማሪም፤ የACPS የ‘2022-23 Back to School’ መምሪያ ለቤተሰቦች - ጥሩ የመረጃ-ምንጭ ነው።

## ለተማሪዎች፣ በትምህርት ቤት ምግቦች ላይ መወሰድ-የሚገባው እርምጃ



የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) - የትምህርት ቤት አመጋገብ አገልግሎቶች ቡድን (School Nutrition Services team)፤ ለሁሉም ቤተሰቦች፤ በተቻለ-ፍጥነት፣ ልክ-ማድረግ እንደቻላችሁ - የተማሪ ምግብ አካውንቶችን እንዲመዘግቡ (set up እንዲያደርጉ) ያበረታታል። ለቤተሰቦች፣ በኢሜል አማካኝነት ወይም በአሜሪካ ፖስታ/ቤት (U.S. Mail) አገልግሎት አማካኝነት፤ ከተማሪ የመታወቂያ (ID) ቁጥር እና የ’ፒን’ (PIN) ቁጥር ጋር - የተማሪ አካንውንት ለትምህርት ቤት ምግቦች እንዴት በመመዝገብ (set up በማድረግ) ማሰራት እንደምትችሉ የሚያሳየው-የመመሪያ ትዕዛዞች፣ ተልኮላችኋል። ቤተሰቦች ወደ አካውንቱ፤ ገንዘብ መጨመር፣ የተማሪውን የግዢ ሁኔታ መቆጣጠር፣ እና ወደ ነፃ እና ቅናሽ-

ዋጋ የተደረገላቸው ምግቦች (Free and Reduced-Price Meals (FARM) - ለFARM ማመልከቻ ሂደትን ለማካሄድ የሚያገለግለውን ማገናኛ (link)ን በመጠቀም በኦንላይን ማመልከት ይችላሉ።

በ2022-23 የቀለም-ትምህርት ዓመት ወቅት የሚገኙ ሁሉም የምግብ አገልግሎቶች፤ ከወረርሽኙ-በፊት ወደ-በነበረው የክንውን-ሂደቱ የሚመለስ ይሆናል። ተማሪዎች፤ [የACPS Community Eligibility Provision (CEP) ከሆኑት ስምንት ትምህርት ቤቶች ውስጥ በአንደኛው-ውስጥ] የማይማሩ፤ ወይም ለ'FARM' ብቁ-ያልሆኑ፤ ለቁርስ እና ምሳ ምግቦች ክፍያ-የሚከፍሉ ይሆናል፤ እና ቤተሰቦች ወደ ተማሪው አካውንቶች ውስጥ ገንዘብ መጨመር ያስፈልጋቸዋል። ማንኛውም ከዜሮ-በታች የሆነ የተማሪ የምግብ አጠቃላይ የገንዘብ-መጠን የነበረው ሁሉ፤ ሁሉን ተሰርዞ-የጠፋ እና ተመልሶ-ወደ $0.00 እንዲሆን ተደርጓል።

የ'FARM' ማመልከቻዎችን ለ2022-23 የትምህርት ዓመት የሚያስገቡበት የመጨረሻ-ማብቂያ ቀን፤ **ሴፕቴምበር (Sept.) 8 ቀን 2022** - የተስተካከለ የቀን-መቁጠሪያ (modified calendar) ለሚከተለው ለሣሙኤል ተከር (Samuel W. Tucker ) የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲሆን፤ ለACPS ትምህርት ቤቶች የ'FARM' ማመልከቻዎችን የማስገቢያ-የመጨረሻ ማብቂያ-ቀን **ኦክቶበር (Oct.) 6 ቀን 2022** ነው። ለተማሪ ምግቦች - የገንዘብ እርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ቤተሰቦች፤ ለ2021-22 የትምህርት ዓመት - ለነፃ እና ቅናሽ-ዋጋ የተደረገላቸው ምግቦች (Free and Reduced-Price Meals) ብቁ-ሆነው የነበሩ ወይም በ 'CEP' ትምህርት ቤት ውስጥ ባለፈው ዓመት የተማሩ፤ የ'FARM' ማመልከቻ ቅጾችን አጠናቀቆ ለማስገባት - ተጨማሪ የ30-ቀን የሚኖራቸው ይሆናል።

በ2022-23 የትምህርት ዓመት - የትምህርት ቤት ምግቦች የክፍያ-ዋጋ፣ እንደሚከተለው ነው:

- ከK-12 ክፍሎች-ውስጥ ለሆኑ - ቁርስ: $2.00
- ከK-5 ክፍሎች-ውስጥ ለሆኑ - ምሣ: $3.05
- ከ6-12 ክፍሎች-ውስጥ ለሆኑ - ምሣ: $3.25
- የአዋቂ (Adult) ምግቦች: $4.00

የ'Menu calendars'፤ ከK-5 ክፍሎች ውስጥ ለሚገኙ ለእያንዳንዱ ቤተሰቦች የሚሰጥ ይሆናል። በተጨማሪም 'menus' በትምህርት ቤት የአመጋገብ አገልግሎቶች፣ አፕ (app) አማካኝነት፣ እና [በACPS ድህረ-ገጽ] ላይ የሚገኙ ይሆናል።

## የኦገስት (August) - የ'ACPS' ተማሪ እና ሠራተኛን እውቅና-መስጠት




ከዚህ ዕትም ጀምሮ፤ የ*'ACPS Express'* እና የ*'ACPS Insider'*፣ በACPS ተማሪዎች እና ሠራተኞች ያገኟቸውን - በርካታ ድንቅ-ስለሆኑ ሽልማቶች፣ እውቅና-መስጫዎች እና የተገኙ የክብር-ሽልማቶች (honors achieved)ን የሚገልጽ ዜና፣ በወርሃዊ የእውቅና-መስጫ አምድ-ሥር የሚገለጹ-ይሆናል። አስደናቂ-የሆነ ውጤታማነታቸው፤ የትምህርት ቤት ክፍላችን/school division በኩራት-ጎልቶ እንዲታይ እና፣ እኛም በጣም እንኮራባቸዋለን!



## የአሌክሳንድርያ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Alexandria City High School) አስተማሪ፣ ተሬሳ ቻቪስ (Teresa Chavis)

ተሬሳ ቻቪስ (Teresa Chavis) - በአሌክሳንድርያ ከተማ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Alexandria City High School) ውስጥ የፋሽን የግብይት (fashion marketing) አስተማሪ የሆኑት፤ የ'Virginia Association of Marketing Educators (VAME) 2022' - የዓመቱ ምርጥ አስተማሪ ሆነው፣ ምአግኘት የሚገባቸው ክፍል አግኝተዋል። "የመጀመሪያ አፍሪካዊ-አሜሪካዊ በመሆን ይህን በማግኘቴ ክብር እና ኩራት ይሰማኛል፣" ቻቪስ (Chavis) ብለዋል። "ይህን-ስራ የምሠራው፣ ለምናገለግላቸው ተማሪዎች ነው፣" በለው አክለዋል። ቻቪስ (Chavis) በተጨማሪም፤ የ20 ዓመታት በትምህርት-ሰጪነት አገልግሎት ሽልማታቸውንም ተቀብለዋል።

የ'VAME' የዓመቱ ምርጥ አስተማሪ፤ እውቅና-የሰጠው - ለግብይት ትምህርት (marketing education) እንዲሁም ለማህበረሰባቸው፣ ትምህርት ቤት እና ለተማሪዎች ቁርጠኝነት-ያሳዩ፣ የማኅበር አባላቸው ነው። በACHS ውስጥ - እንደ በአሁኑ-ጊዜ የሚገኝ የግብይት ቡድን (marketing team) መሪ በመሆን፤ ቻቪስ (Chavis) - ግብይት (marketing)፣ የላቀ-ደረጃ ያለው የግብይት ኢኮኖሚክስ እና የግል-ገንዘብ አያያዝ፣ እንዲሁም ስፖርት እና የመዝናኛ ግብይት (entertainment marketing)ን አስተምረዋል። በአሁኑ-ጊዜ፤ የፋሽን ግብይት (fashion marketing)፣ የላቀ-ደረጃ ያለው የፋሽን ግብይት እና ወደ ፋሽን የስራ-መስኮች መስተዋወቂያን እያስተማሩ ያሉ እና የ'ACHS የFashion Club' አድቫይዘርም ናቸው። ቻቪስ (Chavis)፣ ለ14 ዓመታት የ'VAME' አባል የሆኑ እና በቦርዱ ውስጥም ለስድስት ዓመታት አገልግለዋል።

ቻቪስ (Chavis)፣ በ'fashion merchandising' - 'business administration'ን ማይነር/minor አድርገው፤ ከUniversity of Maryland Eastern Shore - ባችለር ኦፍ ሳይንስ አላቸው። በትምህርታዊ አስተዳደር - ከ'Trinity Washington' ዩኒቨርስቲ፤ የማስተርስ-ዲግሪንም የያዙ-ናቸው። በ'Fashion Institute of Design and Merchandising' ውስጥ፣ የበጋ (summer) የ 'fashion track' ፕሮግራምን አጠናቅቀዋል።

ቻቪስ (Chavis)፣ ፋሽንን እና በሚቀጥለው ትውልድ (next generation) እይታ ማስተማርን የሚወዱ-ናቸው። ስለ 'VAME' እውቅና የተሰማቸውን አጠቃለው ሲናገሩ፤ የቀድሞ የ'U.S. Secretary of State' ኮንደሊዛ ራይስ (Condoleeza Rice)ን አንድ-ጊዜ ያሉትን በመጥቀስ-ነበር፤ "People who end up as 'first' don't actually set out to be first. They set out to do something they love."




## የACHS፣ ሚኒ ሃዋርድ (Minnie Howard) ተማሪ፤ ጃሚካ ሬንዶርፍ (Jammica Reindorf)

ጃሚካ ሬንዶርፍ (Jammica Reindorf) - በአሌክሳንድርያ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Alexandria City High School (ACHS) - ሚኒ ሃዋርድ ካምፓስ (Minnie Howard Campus) ውስጥ በዚህ በልግ (fall) ዘጠነኛ ክፍልን የምትጀምር ስትሆን፤ የመጣችውም ከፍራንሲስ ሲ. ሃመንድ (Francis C. Hammond) መካከለኛ (Middle) ትምህርት ቤት እና ከዊሊያም ራምዚ (William Ramsay) የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው። የ'Advancement Via Individual Determination (AVID)' ፕሮግራም አንዱ-አካል የሆነች፣ እና በ'AVID Eastern Division' እና በ'Mid-Atlantic Southern States Area' ቡድን - የ'AVID Summer Institute/Paths' ንግግር-አድራጊ ተማሪ ሆና በድርጅቱ የጁላይ (July) ዝግጅት፣ በBaltimore ውስጥ ተመርጣ-ነበር። ሬንዶርፍ (Reindorf) - በአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) ውስጥ - በዓመታዊው የ'AVID' ክልላዊ ወይም ብሄራዊ የበጋ (summer) ስልጠና ዝግጅት ውስጥ - ክፍሉ/division ከ'AVID' ጋር አጋርነትን  በ2009 መፍጠር ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ፤ የመጀመሪያዋ ተናጋሪ ሆና የተመረጠች ናት። "AVID ቀላል-የሆነ የአራት-ፊደላት ምዕፃረ ቃል ብቻ ወይም የመማሪ-ክፍል ብቻ አይደለም፤ ነገር ግን የወደፊት ህይወቴ መሠረትም ጭምር… ከእኩዮቼ ለየት-ያልኩ ነበርኩ ግን እንዴት ምኞቴን ማሚላት እንደምችል አላውቅም ነበር፤ እና በድንገት 'AVID' ወደሕይወቴ መጣ፣ ብላለች ሬንዶርፍ (Reindorf) - ከ1,700 በላይ ትምህርት-ሰጪዎች በተሰበሰቡበት ላይ ንግግር-ስታደርግ።

በግንኙነት አቅም-መሠረት ላይ ትኩረት ያደረጉት - የሬንዶርፍ (Reindorf) ለ'AVID' ከመረጡ አስተማሪዎች በተጨማሪ፤ በመጀመሪያ-ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ጀምሮ፤ ወደ አሜሪካ ከመጣን-ጀምሮ - መጠነ-ሰፊ የሆነ የመማር ዕድሎችን ማግኘቷን እርግጠኛ በመሆን የሰራችው እናቷ እንደሆነች ተናግራለች። በጋና (Ghana) ውስጥ ያደገች እና አሁን-ደግሞ በአሜርካ እያደገች-ያለችው ሬንዶርፍ (Reindorf) እንዳለችው፤ እናቷ ሁልጊዜ ያላትን ችሎታ በሚገባ-እንድታጎለብት ደጋግማ-ትነግራት እንደነበር ተናግራለች። ከጊዜ-በኋላ፣ ሬንዶርፍ (Reindorf)፤ በቀለም-ትምህርት ላይ የበለጠ እራሷን-ችላ እንደምትሰራ ያወቀች እና፣ እናቷም የእርሷን መልካም-ፍላጎት በመጠበቅ ቆይታለች። ሬንዶርፍ (Reindorf) በመጨማርም፤ "በ'AVID' ላይ መስራት እና ከ'AVID' የሚጠበቁትን-ደረጃዎች መጠበቅ - ቀላል ነበር፤ ምክንያቱም - ጠንክሮ-የመስራትን ጠቃሚነት ስለተገነዘቡት ነው።' ብላለች።

ሰላሳ-ስምንት የ'ACPS AVID' ትምህርት-ሰጪዎች እና አመራሮች፤ ከሬንዶርፍ (Reindorf) ጋር ሆነው - ወደ 'Baltimore' ከ'AVID' ቡድን ጋር አብረው-ከተጓዙ ከእናቷ እና ከእህቷ ጋር በመሆን በጁላይ (July) ዝግጅት ወቅት አክብረዋል።

## እንኳን ደስ-አለዎት፤ ለአዲሱ የተቋማት ዋና ዳይሬክተር ኤሪካ ጉሊክ (Erika Gulick)



የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) - ከ2020 ጀምሮ በACPS የካፒታል ፕሮግራሞች ዕቅድ እና ዲዛይን ዳይሬክተር ሆኖ ሲያገለግሉ የነበሩት፤ ኤሪካ ጉሊክ (Erika Gulick) እንደ አዲስ የተቋማት ዋና ዳይሬክተር ሆነው መሾማቸውን ሲያሳውቅ-ደስታ ይሰማዋል። ጉሊክ (Gulick) - ወደ ACPS የተቀላቀሉት በ2015 እንደ የተቋማት ዕቅድ-አውጪ (GIS specialist) ሆነው እና፣ በ2018 ወደ ሲኒየር ዕቅድ-አውጪ (senior planner) እድገት-አግኝተ ነበር።

በአዲሱ የስራ-ድርሻቸው በሆነው - ዋና ዳይሬክተር፤ በተቋማት ክፍል በሆነው የተቋማት መምሪያ እና ክንውኖች ውስጥ - የስልታዊ ዕቅድ-አወጣጥ እና ቁጥጥር የበላይ-ተቆጣጣሪ ሆነው የሚሰሩ ሲሆን፤ ይህም - የካፒታል ፕሮግራሞች፣ ዕቅድ-ማውጫ እና ዲዛይን ቢሮ (The Office of Capital Programs, Planning and Design)፣ የትምህርታዊ ተቋማት እና ግጠና፣ እና የእርዳታ-አገልግሎት ሰጪ (Custodial Services) ያካተተ-ይሆናል። በተጨማሪም - ጉሊክ (Gulick)፣ የተቋማት እና ክንውኖች ሹም የሆኑትን ዶ/ር አሊሲአ ሃርት (Dr. Alicia Hart)ን - የተቋማት ቢሮ ዳይሬክተሮችን በመቆጣጠር፣ በመምሪያው ውስጥ በሂደት እና በክንውን ማሳደግ ላይ የሚረዱ፣ እና ለሁሉ ከተቋም-ጋር ግንኙነት ያላቸውን ይዘቶች ረጅም-ስፋት ያለው ዕቅድን በመርዳት፤ የሚያግዟቸው ይሆናል።

“የጉሊክ (Gulick) - በዕቅድ-አወጣጥ፣ በጀት፣ በተቋማት እድገት እና ባለድርሻ-አባላትን በመቆጣጠር ላይ ባላቸው የላቀ-ልምድ፤ እንዲሁም ይህን የስራ-ድርሻ በመውሰድ - በአዲስ ግንባታ፣ እድሳት እና ግገር ላይ - መጠነ ሰፊ ጥቅሞች ለመመሪያው እና ለትምህርት ቤት ክፍሉ የሚያመጡ ናቸው፣” ብለዋል ሃርት (Hart)። ለካፒታል ፕሮግራሞች፣ ዕቅድ እና ዲዛይን ዳይሬክተርነት ላለው ክፍል የስራ-ድራሻ፤ በመጪው ሣምንታት ውስጥ ብቁ-የሆነ ሰው ፍለጋ ይጀመራል።

## የ‘Back to School’ ጥራዛችሁ (Packet)ን - እስከ ሴፕቴምበር (Sept.) 30 ቀን 2022 ድረስ አጠናቁ




እስከ ሴፕቴምበር (Sept.) 30 ቀን 2022 ድረስ፣ ሁሉም ቤተሰቦች የ‘Back to School’ ቅጾችን ለተማሪዎቻቸው ተሞልቶ-መጠናቀቁን እርግጠኛ መሆን-የሚያስፈልጋቸው ሲሆን፣ ይህን በማድረግ - ትምህርት ቤቶች፣ ለእያንዳንዱ ተማሪ የሚያስፈልጋቸውን መረጃ እንዲያገኙ ያደርጋል። በአደጋ-ጊዜ መገናኘት የሚችሉ ሰዎች አድራሻዎችን፣ የልጆችን የጤና መረጃዎች እና በማንኛውም

የመውጣት (opt-out የማድረግ) ምርጫዎችን በመግለጽ፣ ከሌሎች-በእነዚህ ጥራዞች ውስጥ ጠቃሚ-የሆኑ ነገሮች ጋር፤ እባካችሁ ቤተሰቦች-እንድታረጋግጡልን እንጠይቃለን።

እንግሊዘኛ- እና ስፓኒሽ-ተናጋሪ ቤተሰቦች - ከኤሌክትሮኒክ ዲቫይስ (electronic device) ጋር፤ አስፈላጊ የሆኑትን ቅጾች በ'PowerSchool' ውስጥ ለመሙላት - ከዚህ በታች-ያለውን ማገናኛዎች (links) መጠቀም አለባቸው:

- እንግሊዘኛ/English 2022-23 የ'Back to School' ቅጾች።
- ስፓኒሽ/Spanish 2022-23 የ'Back to School' ቅጾች።

በእንግሊዘኛ-ቋንቋ፤ በ'PowerSchool' ላይ፣ የአሳዳጊ አካውንት የመፍጠሪያ የመመሪያ-ትዕዛዝ - ቪዲዮ ይገኛል።

በተጨማሪም፤ የአማርኛ- እና የአረብኛ-ቋንቋ ተናጋሪ ቤተሰቦች - የታተመ የ'Back to School' ጥራዝ (packet)ን ከልጆቻቸው ትምህርት ቤቶች ለማግኘት እንዲጠይቁ፤ ወይም አማርኛ እና አረብኛ ቅጾችን በኦንላይን ላይ በማግኘት እንዲሞሉ፤ እናበረታታቸዋለን። እንግሊዘኛ- እና ስፓኒሽ-ተናጋሪ ቤተሰቦች - የኤሌክትሮኒክ ዲቫይስ-የሌላቸው (without an electronic device)፤ እነርሱም የታተመ ጥራዝ (packet)ን ከትምህርት ቤቶቻቸው ለማግኘት መጠየቅ፤ ወይም እንግሊዘኛ እና ስፓኒሽ ቅጾችን በኦንላይን ላይ በማግኘት ሊሞሉም ይችላሉ። ተሞልቶ-የተጠናቀቁ ቅጾች፤ ወደ ትምህርት ቤቱ የእንግዳ መቀበያ ቢሮ (front office) መግባት-አለባቸው።

ከዚህ-ቀደም የነበረው የትምህርት ዓመት ላይ የነበረው፣ አሁን-የሚገኘው መረጃ፤ በእያንዳንዱ ተማሪ አካውንት ውስጥ እንደሚቀመጥ፣ እባካችሁን አስተውሉ። በትምህርት ቤት መጀመሪያ-ላይ በዚህ ላይ ምልከታ-ማድረግ ጠቃሚ-ነው፤ ይህም፣ በጣም-በቅርብ ጊዜ የተስተካከለ፣ የእያንዳዱ ተማሪ መረጃ - ACPS እና ትምህርት ቤቶች እንዳላቸው ቤተሰቦች ለማረጋገጥ-ስለሚያስችላቸው ነው።

## ዳሽ (DASH)፤ ካለምንም-ክፍያ ለተማሪዎች መጓጓዣ ያቀርባል




ዳሽ (DASH) አውቶቡሶች፣ በአሌክሳንድርያ ከተማ ውስጥ፣ ከመጓጓዣ-ክፍያ ነፃ የሆነ-ነው። ይህም ማለት፤ የአሌክሳንድሪያ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Alexandria City High School (ACHS) ተማሪዎች፣ አፕ (app)ን መጠቀም ወይም መታወቂያ ካርዳቸው (ID card) ወደ-የዳሽ (DASH) አውቶቡስን ለመሳፈር አያስፈልጋቸውም። ወደ አውቶቡሱ ዝም-ብለው መግባት እና ወደ ትምህርት ቤት መጓዝ እንዲሁም- በቀኑ መጨረሻ ወደ ቤት መመለስ ይችላሉ። በመሠረቱ፣ ሁሉም የ'ACPS' ተማሪዎች፣ ሠራተኞች እና ቤተሰቦች፤ በየቀኑ በከተማው ለመዘዋወር፣ ወደ ትምህርት ቤት በመሄድና በመምጣት - በነፃ ዳሽ (DASH)ን መጠቀም ይችላሉ።

ስለ አዲሱ የ'DASH Network' ተጨማሪ መረጃዎችን ለማግኘት፤ የDASH Network አዲሱን የጉዞ ዕቅድ-ማውጫ፣ የአውቶቡስ-መሄጃ መንገዶችን እና የአገልግሎት ዝርዝር-መግለጫዎችን—እና በስፓኒሽ እና በአማርኛ የተተረጎመውን መረጃ ጨምሮ - ለማግኘት፤ DASH Network ድህረ-ገጽን ጎብኙ።

## ለኦገስት (Aug.) 25 ቀን 2022 - የትምህርት ቤት ቦርድ አጀንዳ



የትምህርት ቤት ቦርድ፣ የ‘Work Session’ በኦገስት (August) 25 ቀን 2022 የሚያዘጋጅ ሲሆን፤ ይህም በ‘የመጪው የትምህርት ዓመት ትኩረት-በሚያስፈልጋቸው ነገሮች ላይ/Areas of Focus for the coming school year’ የቀረበውን-ረቂቅ፤ በማሳያ-ማቅረብን ያካተተ ነው። በተማሪ ማህበራዊ/ስሜታዊነት ጠቋሚዎች፣ በፌደራል ማስተካከያ የተደረገለት የ‘Standard of Learning (SOL)’ ውጤቶች፣ ስር-የሰደደ ከትምህርት ገበታ-መቅረት የመጠን-ተመኖች፣ እና ቀደምት-ደረጃ ያለው የትምህርት ቤት እውቅና-መስጠት ሁኔታውም፤ በማሳያ-ማቅረቢያው (presentation) ውስጥ ይካተታል።

የትምህርት ቤት የቦርድ ስብሰባ አጀንዳዎችን እና ሰነዶችን ለማግኘት፤ Electronic School Boardን ይጎብኙ። ስብሰባዎችን በቀጥታ ለመመልከት እና ለመካፈል እንዴት እንደሚችሉ መረጃዎችን ለማግኘትም፤ በትምህርት ቤት ቦርድ ስብሰባ ድህረ-ገጽ መጎብኘትም ትችላላችሁ።

## ‘ParentSquare’: ቀላል-ለሆነ ግንኙነቶች/Communications፣ የቤተሰብ አፕ (App)ን ዳውንሎድ አድርጉ!




የአሌክዳንድርያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS)፤ ጠንካራ የሆነ የትምህርት ቤት እና የመኖሪያ ቤት ግንኙነትን ለማበረታታት - አዲስ የግንኙነት መድረክ (communication platform)ን - አስጀምሯል። ParentSquare፤ ለትምህርት ቤት ግንኙነቶች - የተጣመረ አፕ (unified app) ሲሆን፤ ቤተሰቦች - ማስታወቂያዎችን ከክፍሉ እና

ከትምህርት ቤቶቻቸው እና አስተማሪዎች በአንድ-ቦታ እንዲያገኙ፤ በሁለት-መንገድ የግንኙነት-ማድረጊያ፣ በሚመርጡት-ቋንቋ አማካኝነት - የቴክስት መልዕክቶች፣ የኮንፈረንስ የጊዜ-ሰሌዳ ማያዣ እና የመመዝገቢያ (sign-ups ማድረጊያ) ውስጥ ለማሳተፍ ተጨማሪ ዕድል የሚሰጥ ነው።

ቤተሰቦች፤ በሦስት ቀላል-እርምጃዎች መጀመር-ይችላሉ:

1. የ'ParentSquare' አፕ (app)ብ ከiOS ወይም አንድሮይድ (Android) ዲቫይሶች፤ ከ Apple App store ወይም Google Play ስቶር (store)፣ ዳውንሎድ ማድረግ።
2. ወደ 'ParentSquare'፣ ማግባት (Log in ማድረግ) - ለትምህርት ቤታችሁ(ቤቶቻችሁ) የሰጣችሁትን የኢሜል አድራሻ ወይም የሞባይል ስልክ (cell phone) ቁጥርን በመጠቀም ማግባት (log in ማድረግ)እና የመገኛ አድራሻውን (contact information)ን ማረጋገጥ።
3. ለተማሪዎ አስፈላጊ-የሆኑ ፖስቶች (posts)ን መቀበል-ጀምሩ።

የ'ParentSquare'፤ ግንኙነቶችን ማስተላለፍ የሚችል እና፣ በትምህርት ቤት ማህበረሰቡ ውስጥ የሚገኙ ሁሉንም ኃይል-እንዲኖራቸው በመርዳት - ግንኙነት አድርገው እና መረጃ-እያገኙ እንዲቆዩ ያደርጋል። በ'ParentSquare' - ቤተሰቦች፣ የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ:

- በኢሜል፣ ቴክስት፣ ወይም በሞባይል አፕ (mobile app) አማካኝነት፣ ከትምህርት ቤት መልዕክቶችን መቀበል።
- መረጃዎች በመጡ-ጊዜ (ወዲያውኑ/Instant) ለማግኘት፣ ወይም ሁሉንም-በአንድ ላይ ወደ 6 p.m. አካባቢ-ላይ፣ (Daily Digest)ን እንድታገኙ መምረጥ።
- በሚመርጡት-ቋንቋ፣ ግንኙነቶችን ማደረግ።
- በአውቶማቲክ ማስተርጎም - ከሠራተኞች ጋር፤ የሁለትዮሽ የቴክስት መልዕክቶችን መላክ።
- በትምህርት-ገበታ ላይ የመገኘትና አለመገኘት (attendance) ማስታወቂያዎችን፤ የተማሪውን የመቅረት-ፈቃድ መጠየቂያ ማስታወሻን በዲጂታል የመላክ-አማራጭን ይዞ - መረጃዎችን መቀበል።
- ለወላጅ-አስተማሪ ኮንፈረንሶች፣ መመዝገብ (Sign up ማድረግ)።
- ፈቃድ-የመስጫ ወረቀቶችን (permission slips) እና ሌሎች ተጨማሪ-ነገሮችን መፈረም፤ ሁሉንም ከኮምፒውተር ወይም ከሞባይል ዲቫይሳችሁ ማድረግ።

በአዲሱ የትምህርት ዓመት ከACPS ግአር ግንኙነት ለማድረግ ዝግጁ መሆናችሁን - እርግጠና ሁኑ — አፕ (app)ን አንድ-ጊዜ ዳውንሎድ ካደረጋችሁት ከPreK-12 ከፍል ድረስ ልትጠቀሙት-ትችላላችሁ! በ'ParentSquare' ላይ አጠቃላይ የቪዲዮ ምልከታ - በእንግሊዘኛ እና በስፓኒሽ መገኘት-ይችላል። የአማርኛ እና የአረብኛ ቪዲዮዎች፤ በቅርቡ-እንድታገኙ ይደረጋል።

## ለአዲሱ የትምህርት ዓመት፣ የACPS ቤተሰቦች እንዲዘጋጁ መርዳት



የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS)፤ ለ2022-23 የትምህርት ዓመት ጠንካራ-የሆነ አጀማመር - ቤተሰቦችን የሚያስፈልጓቸውን መረጃዎች በቀላሉ እንዲያገኙ ለመርዳት እዚህ ይገኛል።

የሚከተለው መረጃ አካትቶ የያዘው፤ አስፈላጊ-የሆኑ የመረጃ-ምንጮችን እንዲሁም hACPS ጋር ግንኙነት ማድረጊያ ዕድሎችን ይዟል።

ቤተሰቦች፤ ጊዜውን የጠበቀ መረጃን - በትምህርት ቤት ክፍል (school division) ምን እየተካሄደ እንደሆነ ለማወቅ፤ ወደ 'ACPS Express' *አባል-ለመሆን መመዝገብ* ይችላሉ። ጽሁፎቹ የሚገልጹት፤ የACPS አጋርነቶችን እና ተማሪዎቻችን፣ ፕሮግራሞች እና ሠራተኞች - ውጤታማነቶች ላይ ትኩረት ያደረገ፣ እንዲሁም "ልትጠቀሙበት የምትችሉትን ዜና (news you can use)" ማስታወሻዎች እና አዲስና ማሻሻያዎች (updates) የሚያንፀባርቅ ነው።

## የተማሪ፣ የሥነ-ምግባር ደንብ (Code of Conduct)

ሁሉም ቤተሰቦች፤ የACPS የተማሪ፣ የሥነ-ምግባር ደንብ (Code of Conduct)ን እንዲመለከቱ-ምክር የሚሰጣቸው፤ እና ተማሪዎች - የትምህርት ቤት አካባቢውን በደህንነት በመጠበቅ ላይ እንዳሉ፣ መማርን በሚያበረታታ ባህሪዎች ውስጥ እንዲሳተፉ ይበረታታሉ። ተማሪዎች - የማህበራዊ፣ ስሜታዊ እና የቀለም ትምህርት ችሎታዎችን ለመገንባት መርዳት፤ በትምህርት ቤታችን ማህበረሰብ ውስጥ - በመማር ሂደቱ ውስጥ በጣም ስኬታማ ለመሆን የሚያስፈልጋቸው ጠቃሚ ክፍል ነው።

## ትምህርት ቤት እና መኖሪያ ቤትን የሚያገናኝ - የቤተሰብ የግንኙነት-ክፍል

የቤተሰብ የግንኙነት-ክፍሎች (Family liaisons)፤ ከዚህ-ቀደም የወላጅ የግንኙነት-ክፍሎች (parent liaisons) ተብሎ-ይታወቅ የነበረው፤ በትምህርት ቤት ክፍል (school division) መካከል ግንኙነቶችን ለማሳደግ ረድቷል። በቤተሰቦች እና በትምህርት ቤቶቻችን መካከል ዕምነትን ለማሳደግ፤ የግንኙነት ክፍላችን - ለቤተሰቦች የሚያስፈልጓቸውን መረጃዎች እና እረዳታዎችን እንዲያገኙ በማድረግ፤ የተማሪያቸው የቀለም-ትምህርት እና የማህበራዊ ስሜታዊነት ስኬታማነት - በትምህርት ቤት ውስጥ እና ከዚያም-ባለፈ መልኩ፣ እንዲረጋገጥላቸው ለማድረግ ይሠራሉ። ACPS፤ ስምንት በትምህርት ቤት ውስጥ መሠራት ያደረጉ የግንኙነት ክፍሎች (liaisons)፣ እና አራት በክፍሉ-ዙሪያ (divisionwide) የሚገኙ - ሁለት-ቋንቋ የሚናገሩ የግንኙነት ሠራተኞች አሉት።

- ተስፋዬ አምበርብር (Tesfaye Amberber)፤ የአማርኛ ቋንቋ (በክፍሉ-ዙሪያ/divisionwide)
- ናሲባ ቤንግሃነም (Nassiba Benghanem)፤ የአረብኛ ቋንቋ (በክፍሉ-ዙሪያ/divisionwide)
- አድሪያና ኦልግዊን አልካላ (Adriana Olguin Alcala)፤ የስፓኒሽ ቋንቋ (በክፍሉ-ዙሪያ/divisionwide)
- ካሪና ራሞስ (Karina Ramos)፤ የስፓኒሽ ቋንቋ (በክፍሉ-ዙሪያ/divisionwide)

- አና ቦኒላ (Ana Bonilla)፤ አሌክሳንድሪያ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Alexandria City High School)
- ዳሪትዛ ፔርላ (Daritza Perla)፤ ኮራ ኬሊ (Cora Kelly) ትምህርት ቤት፤ ለሂሳብ፣ ሳይንስ ቴክኖሎጂ ቴክኖሎጂ
- ሳልማ አሽማዊ (Salma Ashmawi)፤ ፈርዲናንድ ቲ. ዴይ (Ferdinand T. Day) የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት
- ዲያና ካቫጃል (Diana Carvajal)፤ (Francis C. Hammond) መካከለኛ (Middle) ትምህርት ቤት
- ማሪንስ ላርስ (Marines Lares)፤ ጆርጅ ዋሽንግተን (George Washington) መካከለኛ ደረጃ (Middle) ትምህርት ቤት
- ማይራ ማቲውስ (Myra Matthews)፤ ጄምስ ኬ. ፖልክ (James K. Polk) የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት
- ኒዲአ ሜንአቾ (Nidia Menacho)፤ ጆን አዳምስ (John Adams) የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት
- ሮዛ ላንድሮስ (Rosa Landeros)፤ ማውንት ቨርነን ኮሚውኒቲ (Mount Vernon Community) ትምህርት ቤት
- ሻኔል ጆንስ (Shanell Jones)፤ ፓትሪክ ሄንሪ (Patrick Henry) hK-8 ትምህርት ቤት
- ስቴፋኒ ኤም. ሳንቲዞ-ቦኒላ (Stephanie M. Santizo-Bonilla)፤ ዊሊያም ራምዚ (William Ramsay) የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት

## hACPS ጋር ግንኙነት ማድረግ

ከትምህርት ቤት ክፍል/school division ጋር፣ ቤተሰቦች የሚነጋገሩባቸውን በርካታ መንገዶች አሉ።

- Ask ACPS - ስለ በክፍሉ-ዙሪያ (division-wide) የሚገኙ ጉዳዮች፤ ጥያቄዎች ላሏቸው ቤተሰቦች እርዳታ ይሠጣል። ጥያቄዎችን ማጋራት፣ አስተያየቶችን እና ስጋቶችን በask@acps.k12.va.us አማካኝነት ማቅረብ፤ ለእርዳታ-ከማህበረሰብ ተሳትፎ ቡድናችን ጋር እንድትገናኙ-ያደርጋችኋል። ሚስጢራዊ (confidential) መረጃዎች ከማጋራት፣ እና የትምህርት ቤት አስተዳደሮችን ስለ-ትምህርት ቤትን በተለዩ-ሁኔታ የሚመለከቱ ጉዳዮችን ማነጋገርን ጨምሮ፤ በዚህ በኩል ከመጠቀም እንድትቆጠቡ እንጠይቃለን።

- የACPS በሁለት-ቋንቋ የእርዳታ-መስመር፤ ከትምህርት ቤት ክፍል/school division እርዳታን ለሚፈልጉ ቤተሰቦች - አገናኝ በመሆን ይረዳል። የእርዳታ-መስመሩን (Helpline)፤ ከሰኞ-አርብ፣ ከ10 a.m. እስከ 3 p.m. ድረስ፣ በሚከተሉት ቁጥሮች ቴክስት (text) ማድረግ ወይም መደወል ይቻላል:
    - ለእንግሊዘኛ ቋንቋ፣ በ703-844-1763 ቴክስት (text) አድርጉ ወይም ደውሉ
    - ለስፓኒሽ ቋንቋ፣ በ703-844-3424 ቴክስት (text) አድርጉ ወይም ደውሉ
    - ለአማርኛ፣ በ703-927-6866 ቴክስት (text) አድርጉ ወይም ደውሉ
    - ለአረብኛ፣ በ703-927-7095 ቴክስት (text) አድርጉ ወይም ደውሉ

- ስፓኒሽ፣ አማርኛ፣ አረብኛ፣ ፋርሲ፣ እና ፓሽቶ ከሚናገሩ፤ በቀጥታ-መስመር ላይ የሚገኙ አስተርጓሚዎች - ከትምህርት ቤቱ ጋር በስልክ-ላይ እንዳሉ ሊቀርቡ ይችላሉ። የACPS' toll-free ቁጥርን በ 1-833-611-1667 ደውሉ፣ እና ለትምህርት ቤቱ የተመደበውን የቋንቋ ኮድ (language code) አስገቡ።

## የአሌክሳንድርያ የፒቲኤ (PTA) ካውንስል

የአሌክሳንድርያ የፒቲኤ (PTA) ካውንስል (Alexandria PTA Council (PTAC)፤ ለሁሉም የ'ACPS' ተማሪዎች እና ቤተሰቦች፤ ወኪል-ተከራካሪ ድምፅ፣ እና ሃሳቦችን ለመቀያየር እና በትምህርት ቤታችን ማህበረሰብ ውስጥ ተሳታፊ ሆኖ ለመቆየት - ግሩም-የሆነ ኔትወርክ ሆኖ የሚያገለግል ነው። በስብሰባ የጊዜ-ሰሌዳዎች እና በተጨማሪ ነገሮች ላይ፣ የበለጠ መረጃ ለማግኘት፤ Alexandria Council of PTAsን ጎብኙ።

## በACPS ውስጥ የሚገኙ በራሪ-ወረቀቶች (Newsletters)

የትምህርት ቤት ክፍላችን፣ ለባለድርሻ-አባላት (stakeholders) ለሚፈልጓቸው ልዩ-የሆኑ መረጃዎች - በልዩ-ሁኔታ የተዘጋጀ የመረጃ-ምንጮች እና በራሪ-ወረቀቶች (newsletters) አለው።

- አን አር. ሊፕኒክ (Anne R. Lipnick) - የልዩ ትምህርት (Special Education) የወላጅ የመረጃ-ምንጭ ማዕከል (Resource Center) (PRC)፤ በአሌክሳንድርያ ከተማ ውስጥ፣ ስብጥር-ያላቸውን - ከጉዳተኝነት ጋር የሚገኙ ልጆች ያሏቸው ቤተሰቦችን - በልጆቻቸው-ትምህርት ላይ ተጠሪ-ተከራካሪ ለመሆን የሚያስፈልጓቸውን መረጃዎችን በማቅረብ ያገለግላል። በዝግጅቶቻቸው፤ በዚያው-ጊዜ የማስተርጎም አገልግሎት (Simultaneous interpretation) የሚገኝ ይሆናል። የ'PRC newsletter'፤ ዌቢናሮች/webinars፣ አውደ-ጥናቶች/workshops፣ የምርምር-ጥናቶች እና ልዩ ዝግጅቶችን እና እንቅስቃሴዎችን ጨምሮ፤ ቤተሰቦችን በዝግጅቶች ላይ ያሉ አዲስና-ማሻሻያዎች (updates)ን ያቀርባል።

- The Capital Improvement Program (CIP) newsletter፤ ስለ ACPS የካፒታል ዕቅድ ፕሮጀክቶች (capital planning projects) - ማህበረሰቡ መረጃ-እያገኘ እንዲቆይ ያደርጋል። በየወሩ፤ በመጀመሪያው ሰኞ ቀን የሚወጣውን በራሪ-ወረቀት (newsletter) ለማግኘት፤ ተመዝገቡ (Sign up አድርጉ)።

## ቁልፍ-የሆነ አዲስና-ማሻሻያዎች (Updates) - በተማሪ ጤናማነት፣ በደህንነት እና ጥበቃ ማሳደጊያዎች፤ እና የACPS ድህረ-ገጽ



ለ2022-23 የትምህርት ዓመት ዝግጅት እያደረግን ባለንበት ጊዜ፤ አስፈላጊ-በሆኑ ነገሮች ዙሪያ - እንደ ጤናማነት፣ የትምህርት ቤት ደህንነት እና ጥበቃ፣ የትምህርት ቤት ምግቦች እና ድህረገጾች ባሉ ነገሮች ላይ፣ አንዳንድ ለውጦችን እና አዲስና-ማሻሻያዎች (updates)ን - ከቤተሰቦች ጋር ለማጋራት እንወዳለን።

### የተማሪ ጤናማነት፣ የትምህርት ቤት ደህንነት እና ጥበቃን ማሣደጊያዎች

የተማሪዎቻችንን መልካም-ፍላጎትን መጠበቅን በአዕምሮአችን ውስጥ በማድረግ፤ በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት ውስጥ፣ ለሁሉም ተማሪዎች በማህበራዊ፣ ስሜታዊ፣ እና የቀለም ትምህርት (Social, Emotional, and Academic Learning (SEAL) ውስጥ - ለ30 ደቂቃዎች በየቀኑ በተመደበ ሰዓት ውስጥ ይካፈላሉ። እንደ ማህበረሰብ ዙሪያ (community circles) ያሉ መዋቅሮች፤ የRULER ስርዓተ ትምህርት ከ'የል ማዕከል - ለስሜታዊ ማስተዋልና ግንዛቤ (Yale Center for Emotional Intelligence)' የቀረበውን ለማስራጨት፣ እና አዎንታዊ የሆነ የባህሪይ ጣልቃ-ገብነቶችን እና እርዳታዎችን ለማጠናከር፣ ጥቅም-ላይ ይውላል። የእያንዳንዱ ትምህርት ቤት የተማሪ እርዳታ ቡድን (Student Support Team) በበኩሉም፤ የበለጠ ዒላማ-ያደረገ እና ጠንከር-ብሎ የሚሰጡ የአነስተኛ-ቡድን (small group) እና የእያንዳንዱ-ግለሰብ ጣልቃገነነቶች (individual interventions)ን፤ በባለብዙ ደረጃዎች የስርዓት እገዛ (Multi - Tiered System of Support) (MTSS) ሂደት አማካኝነት፣ በዚህ ተለይተው-ለወጡ ተማሪዎች ይሠጣል። በተጨማሪም - የDevereux Student Strengths Assessment (DESSA)ን - የማህበራዊ-ስሜታዊነት መሣሪያን በመጠቀም፤ የየግል እና በጋራ-በአንድነት በመሆን፣ ጠንካራ-ጎኖችን ለመለየት እና ለማሳደግ - ተማሪዎች ይገመገማሉ።

ግንኙነቶች እና የካምፓስ ደህንነትን ማጠናከሪያዎች፤ ሲከናወኑ-የቆዩ እንዲሁም - የ2022-23 የትምህርት ዓመት በሚጀምር ጊዜ መከናወኑ የሚቀጥል-ይሆናል። ሁሉም በአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) ውስጥ የሚገኙ ትምህርት ቤቶች፤ ለተማሪዎች መግቢያ፣ የሠራተኛ እና የጎብኚ-እንግዶች መግቢያን በመመደብ፤ ደህንነትን ለመጠበቅ እና ወደ ተቋሙ መግቢያዎች ቁጥጥር-የተደረገባቸው እንዲሆኑ ለማረጋገጥ እንዲረዳ መድቧል።

ተመራጭ የደህንነት-ጥበቃ ተሞክሮዎችን በምናጠናክርበት ጊዜ፤ ሁሉንም በሁለተኛ-ደረጃ (በመካከለኛ እና በከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት) ውስጥ ያሉ ተማሪዎች - በየቀኑ፤ የተማሪ መታወቂያቸውን እንዲያሳዩ ይጠየቃሉ። ይህ ልምድ፤ በትምህርት አሰጣጡ ሰዓታት ወቅት፣ የተመዘገቡ ተማሪዎች ብቻ ካምፓስ ውስጥ ለመግባት እንደሚችሉ - የህንፃው አስተዳደሮች እና የጥበቃ-ሹሞች ለማረጋገጥ እንዲችሉ ያደርጋቸዋል።

ከACPS ጎብኚ-እንግዳ ፖሊሲ (Visitor Policy) ጋር ተያያዥ የሆነው የጤና እና የደህንነት ጥበቃ እርምጃዎች - አዲሱን የትምህርት ዓመት በምንጀምርበት ጊዜ ውስጥ በስራ-ላይ ይውላል። ቤተሰቦች፤ ወደ ለሁሉም ክፍት የሆነ ዝግጅቶች (Open House events) ተገኝተው መካፈል-የሚችሉ፤ እና አንድ-ጊዜ ትምህርት ከተጀመረ - ጎብኚ-እንግዶች፣ በትምህርት ሰዓታት ውስጥ በእንግዳ-መቀበያ ቢሮ (front office) አካባቢ መመዝገብ (sign in ማድረግ) ይችላሉ። ሁሉም ጎብኚ-እንግዶች፣ በአሁኑ ጊዜ ያለውን

የACPS የጤና እና የደህንነት-ጥበቃ መመሪያዎችን መከተል ያስፈልጋቸዋል። በመጀመሪያው የትምህርት ቀን ላይ፣ ፎተግራፎችን ማንሳት እና ከተማሪ ጋር መሰነባበትን - የህንፃው መግቢያ በዚያን-ቀን ብዙ መጨናናቅ ስለሚበዛበት፤ ተማሪዎች ወደ ህንፃው ከመግባታቸው በፊት-እንድታደርጉት - እባካችሁ አስታውሱ።

ACPS፣ የዲጂታል የተማሪ መታወቂያ (digital student identification (ID) የሙከራ ፕሮግራምን፣ በከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ካምፓሶች ለማካሄድም እያቀደ-ነው፤ ይህ ፕሮግራም ተማሪዎች የተለመደውን ዓይነት ወይም የዲጂታል መታወቂያ (digital ID)ን - (በስማርትስልክ/ስማርት ዲቫይስ ላይ የተቀመጠውን) ወደ ትምህርት ቤት በሚገቡ ጊዜ - ስካን (scan) በማድረግ ለመጠቀም አማራጭ ይሰጣቸዋል። የ'ACPS' ሠራተኞችም - በትምህርት ቤቶች ውስጥ፣ በማዕከላዊ ቢሮ፣ እና/ወይም በACPS-ንብረት በሆኑ ቦታዎች ውስጥ፤ የስም-ባጅ (badge) እንደሚታይ አድርገው ማድረግ ያስፈልጋቸዋል። ሌላ የደህንነት ጥበቃ እርምጃ የሆነው፤ በሁለተኛ-ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የትምህርት ቤት አስተዳደሮችን ለማገዝ - የትምህርት ቤት የጥበቃ-ሹሞች (school security officers (SSOs)ን መጨመር ነው።

እባካችሁ አስታውሱ፤ ሁሉም የACPS ትምህርት ቤት ካምፓሶች - ዝግ-የሆኑ ካምፓሶች (closed campuses) ናቸው። "ዝግ-የሆነ ካምፓስ (Closed Campus)" ማለት፤ የምሣ ሰዓትን ጨምሮ፣ ተማሪዎች ፈቃድ-ካላገኙ በስተቀር፤ መምጣት እና መሄድ አይፈቀድላቸውም።

በተጨማሪም፤ ሁሉንም የግንኙነት-መስመሮች ክፍት አድርጎ ለመቆየት፤ ACPS - የሕዝብ ማስታወቂያ መስጫ ዘዴዎችን እና የስልክ ዘዴዎችን በሁሉም ትምህርት ቤቶች ውስጥ - በበጋው (summer) ወቅት ጊዜ ጠግኖ-ያዘጋጀ እና፣ በትምህርት ዓመቱ ውስጥ - የትምህርት ቤት የግንኙነት ማድረጊያ ዘዴዎችን ለመቀየር - የጊዜ-ሰሌዳ ይዟል። የገመድ-አልባ የመገናኛ መስመር አገልግሎት (cellular service)፤ በአሌክሳንድርያ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Alexandria City High School (ACHS) ኪንግ ስትሪት ካምፓስ (King Street Campus) ውስጥ በዚህ በጋ (summer) የማስፋፊያ ስራ ተደርጎለታል።

ስለእነዚህ ጠቃሚ-የሆኑ የ'ACPS' አዲስና ማሻሻያዎች (updates) እና፣ በተማሪ ጤናማነት፣ ደህንነት እና ጥበቃ ላይ የተደረጉ ማስታወሻዎችን፣ የበለጠ መረጃ ለማግኘት፤ በእንግሊዘኛ፣ ስፓኒሽ፣ አማርኛ ወይም አረብኛ አንብቡ።

## ለACPS እና ትምህርት ቤቶች፤ አዲስ ድህረ-ገጽ

የድህረ-ገጽ መዳሰሻ (Website navigation)፤ በአዲስ-ሁኔታ ዲዛይን የተደረገ ድህረ-ገጽን ለትምህርት ቤት ክፍል፤ እያንዳንዱ የACPS ትምህርት ቤትን ጨምሮ - በማስጀመር፤ የበለጠ-ቀላል እንዲሆን ተደርጓል። አዲሱ ድህረ-ገጽ፤ ለተጠቃሚዎች የበለጠ የተመቻቸ እና በይበልጥ-ለእይታ የሚያምር ሆኖ ተዘጋጅቷል። የ'ACPS homepage'፣ ግልጽ-የሆነ የመግቢያ-መጀመሪያ ነጥቦቹ - ወደ የር ዕሶች ይዘቶች ለማገናኘት - የተጠናከረ ፈጣን-የማገናኛ መስመር (quick-links bar) ከበላይ መደርደሪያ ምስሉ ላይ ያለው ሆኖ የተካተተ፣ እና በተደጋጋሚ ለሚፈለጉ መረጃዎች በቀላሉ መነካት የሚችሉ ምልክቶች (icons) - በቀጥታ ከመደርደሪያ ምስሉ (banner image) በታች ተቀምጧል።

አዲሱ ድህረገጽ፤ በተመቻቸ-ሁኔታ ለመዳሰስ እና ገጽታውን-ጠብቆ ይዘቱን እንዲያገናኝ ሆኑ የበለጠ - ለተጠቃሚዎች ቀላል-የሆነ ተሞክሮ እንዲኖራቸው ተደርጎ ዲዛይን ተደርጓል። ወደ ታች-በሚዘረዝረው አማራጭ (dropdown option) - ከቤተሰብ ክፍል ( family section) ጋር፤ ሁሉም ለትምህርት ዓመቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎች በአንድ-ቦታ የሚገኙ ይሆናል። የ2022-23 የ'Back to School' ገፃችንን፣ እና የትምህርት ቤት እና የክፍል/division - የቀን መቁጠሪያዎችን - ጠቃሚ-የሆኑ መረጃዎች እና ቀናቶችን ለማግኘት፤ ተመልከቱ። ቤተሰቦች፤ ከተወሰኑ የትምህርት ቤት ዜናዎች ጋር ግንኙነታቸው ሳይቋረጥ - የእያንዳንዱ ትምህርት ቤት ድህረ-ገጽ በመጎብኘት በግንኙነት መቆየት ይችላሉ።

በድህረ-ገጹ ላይ ከተጨመረው አንዱ አስደሳች-ገጽታ ውስጥ፤ ቤተሰቦች በከፍተኛ ጥራት ትርጉም በደቂቃዎች ውስጥ እንዲያገኙ የሚያደርገው ነው። አዲሱ የማስተርጎሚያ ዘዴ፤ የበለጠ የተመቻቸ ተሞክሮን ለተጠቃሚዎች ለመስጠት እና የተተረጎመው-ይዘት በበለጠ ትክክለኛነት እንዲቀብ ያደርጋል። ማስተርጎሚያውን ለማግኘት፤ በማንኛውም የACPS ድህረ-ገጽ - በቀን-ማዕዘን በኩል

የሚገኝ እና የአሜሪካ ባንዲራ (U.S. Flag) ባለበት ወይም “English” የሚለው ቃል በመጫን - ወደሚፈልጉት ቋንቋ - ወደታች-ከሚዘረዝረው መምረጫ (dropdown menu) መምረጥ ይቻላል።

ድህረ-ገጹን በድ:ጋሚ-ዲዛይን ማድረግ፤ ግንኙነቶችን የሚያግዝ እና በቤተሰቦች እና በትምህርት ቤቶቻችን እና ክፍል/division መካከል ተሳትፎ-እንዲጠነክር ይረዳል። ቤተሰቦች፣ ተማሪዎች እና ሠራተኞች - ጠንካራ የሆነ ግንኙነቶች ለማዳበር እንዲችሉ የሚረዳ እና፣ ከACPS ፍትሃዊ-እኩልነት ያለው ትምህራዊ ተሞክሮን ከማካሄድ ጋር ጎን ለጎን ይሄዳል።

## ተጨማሪ አዲስና-የተስተካከለ (Updates) - የጤና እና የደህንነት መመሪያዎችን ተመልከቱ፤ እና በቦታ-ላይ ለሚሰጠው የCOVID-19 ምርመራ ለማድረግ ተመዝገቡ




### ተጨማሪ አዲስና-የተስተካከለ (Updates) - የጤና እና የደህንነት መመሪያዎች

ACPS፣ ከበሽታ ቁጥጥር እና መከላከያ ማዕከላት (Centers for Disease Control and Prevention (CDC) ያገኘውን - አዲስና-የተስተካከለውን (updated) የትምህርት ቤት መረጃ የተመለከተው-እና፣ በኦገስት (August) 12 ቀን 2022 የተሰጠውን የCOVID-19 የጤና እና የደህንነት መመሪያዎችን አጠናክሯል። እንደ-ማስታወሻነት፤ ወደ ACPS ህንፃ በሚገባበት-ጊዜ፣ ACPS የሰውነት-ሙቀት መለካት ምርመራን ማድረግ-ከእንግዲህ አያስፈልገውም። ተማሪዎች፣ ሠራተኞች፣ እና ቤተሰቦች፤ ወደ ACPS ተቋም ከመግባታቸው በፊት፣ [ዕለታዊ የህመም ምልክትን መመልከቻ: እራስን-መመርመሪያ]() ምልከታ-ማድረጊያ ጥያቄዎችን በማድረግ እንዲቀጥሉ ይበረታታሉ። ACPS፤ የCOVID-19ን በተቋሞቻችን ውስጥ ያሉ-ታማሚዎችን መቆጣጠሩን ከቤተሰቦቻችን ጋር ሆኖ የሚቀጥል ሲሆን፤ ነገር ግን፣ ለየግል ታማሚዎች የቅርብ-ንክኪ ያላቸውን መከታተል (contact tracing)ን - ከእንግዲህ-አያካሂድም።

ለተማሪዎች፣ ሠራተኞች፣ ጎብኚ-እንግዶች እና በጎ-ፈቃድ ሠራተኞች፤ በትምህርት ቤት ውስጥ እና በአውቶቡሶች ውስጥ፣ ማስክ (Masks) ማድረግ - አሁንም በምርጫ-የሚደረግ (optional) ሆኖ ይቀጥላል። በአዲስና የተስተካከለ (updated) የCDC መመሪያ መሠረት፤ መጋለጡን ከተከሰተ እና ምልክቶችን-ማየት ከጀመሩ ጊዜ ጀምሮ - የቅርብ-ንክኪ ያላቸው (close contacts)– ለሙሉ 10 ቀናቶች የፊት መሸፈኛ ማስክ (mask) እንዲያደርጉ፣ ACPS ይጠይቃል። በተጨማሪም ACPS፣ የቅርብ-ንክኪ ያላቸው (close contacts) ወይ በስድስተኛው ቀን ወይም-ደግሞ ምልክቶችን ማሳየት ሲጀምሩ ምርመራ-እንዲያደርጉ ይጠይቃል። በአንዳንድ-ሁኔታዎች፤ ለCOVID-19 ተጠቂ-እንዲሆኑ የሚያደርጋቸው በሰነድነት የተያዘ የሕክምና ሁኔታዎች ያሏቸው እና በCOVID-19 ከበድ-ያለ ህመም-ሊያስከትልባቸው ይችላል የሚባሉ ተማሪዎች ባሉበት ክፍሎች ውስጥ፤ ሠራተኞች እና ተማሪዎች የፊት-መሸፈኛ ማስክ (masks) ማድረግ-ሊያስፈልግ ይችል-ይሆናል። ሁሉንም - በትምህርት ቤት ማህበረሰባችን ውስጥ የሚገኙትን፣ ለመጠበቅ እርዳታ-በማድረጋችሁ በቅድሚያ እናመሰግናችኋለን።

አሌክሳንድርያ - በመካከለኛ/Medium ወይም ከፍተኛ/High የማህበረሰብ ስርጭት ደረጃ ላይ በሚሆን ጊዜ፤ እንደ CDC መመሪያ መሠረት፤ ACPS፣ የፊት መሸፈኛ ማስኮች (masks) እንዲደረጉ በእጅጉ-ማበረታታቱን ይቀጥላል። እንደ ተጨማሪ እርምጃ ሆኖ፤ በምሣ ጊዜ - ሲመገቡ ተጨማሪ ቦታ እና ርቀት እንዲኖራቸው ለሚፈልጉ ተማሪዎች - ተይዞ-የተቀመጠ የመቀመጫ ክፍሎች/sections ማዘጋጀታቸውን - ትምህርት ቤቶች ይቀጥሉበታል።

ለCOVID-19 በምርመራ ውጤታቸው ቫይረሱ እንዳለ (positive) የሆኑ ግለሰቦች፤ ከCDC በተገኘው የቅርብ-ጊዜ መመሪያ መሠራት፤ አሁንም-ቢሆን መገለል (isolate ማድረግ) ያስፈልጋቸዋል።

- COVID-19 በምርመራ ውጤታቸው ቫይረሱ እንዳለ (positive) የሆኑ ግለሰቦች፤ አስፈላጊ-በሆኑት በ5 የመገለያ-ወቅት በሆኑት ቀናት ውስጥ በትምህርት ቤት ውስጥ ተገኝተው መማር የለባቸውም።
- ቫይረሱ እንዳለ (positive የሆኑ) ግለሰቦች እና ከ6-10 ቀናት ውስጥ ወደ ትምህርት ቤት የሚመለሱ - የፊት መሸፈኛ ማስክ (mask) እንዲያደርጉ ACPS ይጠይቃል።
- በቅርብ-ጊዜ ቫይረሱ እንዳለ (positive ሆነው) የሚመለሱ፣ ወይም በቅርብ-ጊዜ ለCOVID-19 ተጋላጭ-የነበሩ ግለሰቦች፤ ለበሽታ-ተጋላጭነት ያላቸው (immunocompromised) የቤተሰብ አባላቶች ወይም እራሳቸው ለበሽታ-ተጋላጭነት ያላቸው (immunocompromised) ሊሆኑ ስለሚችሉ፤ ለምሣ ተገድቦ-በተቀመጠ ጠረጴዛ ላይ - መቀመጥ የለባቸውም።
- ቫይረሱ ያለባቸው (positive የሆኑ) ግለሰቦች - ከ11ኛው ቀን በፊት የፊት-መሸፈኛ ማስክ (mask) ማድረጋቸው-እንዲያበቃ ለማድረግ፤ ሁለት - ቫይረሱ እንደሌለ (negative) የ'antigen/rapid tests' በ48 ሰዓታት ልዩነት ውስጥ የተወሰዱ - ውጤቶች ወደ reportingCOVID@acps.k12.va.us ማስገባት እንዳለባቸው፤ ACPS ይጠይቃል። ይህ፤ በትምህርት ቤት ውስጥ የCOVID-19 ስርጭትን-ለመቀነስ ይረዳናል።

አሁን ለማንኛው ዕድሜው ከስድስት-ወር በላይ ለሆነ ሁሉ መገኘት የሚችለውን፤ ቤተሰቦች፤ ለተማሪዎች የCOVID-19 ክትባትን እንዲያስከትቡ በእጅጉ-እናበረታታለን። ለተጨማሪ መረጃ እና በአሌክሳንድርያ ከተማ የክትባት ክሊኒኮችን ለማግኘት፤ https:www.alexandriava.gov/Vaccinesን ጎብኙ።

በአሁኑ ጊዜ ስለአለው የጤና እና የደህንነት ጥበቃ መመሪያዎችን ላይ ተጨማሪ መረጃዎች - በaccessed online ላይ መገኘት ይችላል። የታመሙ ተማሪዎች፣ በመኖሪያ-ቤትም ሆነ ወይም በትምህርት ቤት ውስጥ ከታመሙ፤ በACPS Policy JHCF: Student Wellness ውስጥ የተቀመጠውን መመሪያዎች መከተል አለባቸው።

## ነፃ ለሆነው፣ በቦታው-ለሚደረግ የCOVID-19 ምርመራ - ተመዝገቡ

በ2022-23 የትምህርት ዓመት ወቅት፣ በምርመራ-አገልግሎት ሰጪያችን 'Aegis' አማካኝነት - ACPS፣ ሣምንታዊ የCOVID-19 ምርመራን በትምህርት ቤት ቦታው ውስጥ - አሁንም እንደገና በነፃ የሚሰጥ ይሆናል። ለመካፈል-እንዲችሉ፤ ቤተሰቦች እና ሠራተኞች - በ'Aegis' አማካኝነት መመዝገብ ያስፈልጋቸዋል። ላለፈው-ዓመት ወይም በበጋ (summer) ወቅቱ ውስጥ፤ ተማሪዎች እና ሠራተኞች ተመዝግበው የነበረ-ቢሆንም እንኳን፤ ሁሉም-ሰው፣ ለ2022-23 የትምህርት ዓመት - አሁን እንደገና መመዝገብ አለባቸው።

- እባካችሁን፤ ወደ ACPS On-Site COVID-19 Testing ድህረ-ገጽ በመሄድ፤ የእናንተ ቦታ - ለሣምንታዊው ምርመራ፣ አገልግሎት - የሚሰጥበትን ቀን እና ሰዓት ተመልከቱ።
- በ'Aegis' በኩል የሚሰጠው የምርመራ-ዓይነቶች፤ የ'PCR' ምርመራዎች - ከ'አንቲጂን/ራፒድ (antigen/rapid) ምርመራዎች ጋር ነው። ይህም ማለት፤ ምርመራው ከተደረገ በ24 እና 72 ሰዓታት መካከል ባለው-ጊዜ ውስጥ፤ አሁን - የምርመራ-ውጤቶቹን ማግኘት ይቻላል።
- ባለፉት 90 ቀናቶች ውስጥ፣ COVID-19 ይዞት የነበረ ማንኛውም ግለሰብ፤ ከ'Aegis' ጋር በሚደረግ ምርመራ ውስጥ መካፈል-የለበትም፤ ይህም-የሆነበት ምክንያት፤ ምንም እንኳን ከእንግዲህ በሽታውን-አስተላላፊ ባይሆኑም እንኳ - ቫይረሱ-እንዳለ (positive) መሆናቸው ማሳየቱን ሊቀጥል ስለሚችል ነው።
- በትምህርት ዓመቱ ሙሉ-ባለው ጊዜው ውስጥ፣ በሣምንታዊው ምርመራ - ለመመርመር፤ ተማሪዎች እና ሠራተኞች - አንድ-ጊዜ ብቻ መመዝገብ ያስፈልጋቸዋል። በየ-ሣምንቱ መመዝገብ፤ አያስፈልግም።


ቤተሰቦች፤ ተማሪዎችን በ[ACPS ተማሪዎች: የ'Aegis COVID' በሽታው እንዳለ መመርመሪያ (Screening testing) ምዝገባ] ላይ ሊያስመዘግቡ ይችላሉ። የ'ACPS' ሠራተኞች፤ በ[ACPS ሠራተኛ: የ'Aegis COVID' በሽታው እንዳለ መመርመሪያ (Screening testing) ምዝገባ] ላይ መመዝገብ ይችላሉ።

ሁሉም የACPS ትምህርት ቤቶች፤ ከሣሙዔል ተከር (Samuel W. Tucker) የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት በስተቀረ - የCOVID-19 ምርመራን፣ በኦገስት (August) 29 ቀን 2022 ሣምንት-ጀምሮ - የሚጀምር-ይሆናል። ከተከር (Tucker) ምርመራ የሚጀምረው - ከ10 a.m. እስከ እኩለ-ቀን ድረስ - ማክሰኞ - ኦገስት (Aug.) 16 እና ማክሰኞ (Tues.)፣ ኦገስት (Aug.) 23 ቀን 2022 ሲሆን፤ ከዚያም-በመቀጠል፣ ከሴፕቴምበር (Sept.) 1 ቀን 2022 ጀምሮ - በተከር (Tucker) የጊዜ-ሰሌዳ የተያዘለት የምርመራ-ቀን - ሁልጊዜ ሐሙስ ቀን ላይ - ከላይ ባለው በዚሁ በአንድ-ዓይነት ሰዓት ላይ ይሆናል።

በምዝገባ ሂደቱ ላይ ማንኛውም አስቸጋሪ-ሁኔታ በሚገጥም-ጊዜ፤ እባካችሁን ወደ VASchools@testingworks.com ኢሜል አድርጉ። ስለ 'COVID-19 የምርመራ ፕሮግራም' ጥያቄዎች ካላችሁ፤ እባካችሁን፣ የACPS የቅርብ-ንክኪ ያላቸውን መከታተያ ቡድን (ACPS Contact Tracing Team)ን፣ በcontacttracing@acps.k12.va.us ወይም በ 703-619-8082 አነጋግሩ።


በሁሉም ትምህርት ቤቶቻችን እና ማዕከሎቻችን ውስጥ ጤናማ የሆነ አካባቢን ጠብቆ-ለመቆየት አብረን በምንሰራበት-ጊዜ፤ ታላቅ-የሆነ ተለዋዋጭ-ሁኔታዎችን የመቀበል እና አልበገር-ባይነት በማሳየት-የሚቀጥሉ - ሁሉም ቁርጠኛ-ለሆኑ ሠራተኞች እና ቤተሰቦች፤ ACPS ምስጋና-ያቀርባል።

## በኦገስት (Aug.) 11 ቀን - የአሌክሳንድርያ የCOVID-19 ማህበረሰብ ያለበት ደረጃ




እስከ ኦገስት (Aug.) 11 ቀን - ባለው-ጊዜ፤ የአሌክሳንድርያ ከተማ የCOVID-19 ማህበረሰቡ-የሚገኝበት ደረጃ - መካከለኛ ሲሆን፤ ባለፉት ሰባት ቀናቶች ውስጥ፤ በየ100,000 ሰዎች፣ 235.2 ታማሚዎች አሉት። የበለጠ ለማወቅ፤ [Alexandria COVID-19 dashboard] ጎብኙ።

# የመንኪፖክስ (Monkeypox) የመረጃ-ምንጮች እና መረጃዎች፤ ከአሌክሳንድርያ ጤና መምሪያ



መንኪፖክስ (Monkeypox) የቫይረስ ህመም ሲሆን፤ ብዙም የማይታይ-ቢሆንም እንኳ፣ ሰሜን ቨርጅኒያ/ኖርዘን ቨርጅኒያን ጨምሮ - በአሜሪካ ክፍሎች ውስጥ እየታየ-ያለ ነው። የአሌክሳንድርያ ጤና መምሪያ (Alexandria Health Department (AHD) - የመንኪፖክስ (Monkeypox) ድህረ-ገጽ ጠቃሚ-የሆኑ መረጃዎችን እና የመረጃ-ምንጮችን ለሕዝብ ያቀርባል። 'AHD'፣ ከአካባቢ የጤና እንክብካቤ ሰጪዎች ጋር እና ከቨርጅኒያ የጤና መምሪያ ጋር ትብብርን በማድረግ፤ በአካባቢው-የሚደረጉ መመርመሪያ-ቦታዎች መኖርን እና የመንኪፖክስ (monkeypox) ታማሚዎችን በመንከባከብ ላይ፤ ትምህርት እና ዝግጁነት-እንዲኖር ያደርጋሉ። 'AHD' በተጨማሪም፤ ከስቴት እና ከክልል አጋሮች ጋር፤ ከፍተኛ-ስጋት ለሚኖራቸው ግለሰቦች ክትባቶችን-መስጠትን፣ ከግምት-ውስጥ በማስገባት ላይ እየሰራ ይገኛል።

ስለ መንኪፖክስ (monkeypox) የማህበረሰብ ስጋቶች ላይ ምላሽ-ለመስጠት እና ሕዝቡን ለማስተማር በምናደርገው ጥረት፤ የኦንላይን ጥያቄዎች - ወደ ኢሜል alexhealth@vdh.virginia.gov ሊቀርቡ-ይችላሉ። በቀጥታ ከአንድ-ሰው ጋር መነጋገር ከፈለጋችሁ፤ ወደ AHD (703)-746-4988 - በ9 a.m. እና 5 p.m. መካከል ባለው ሰዓት - ከሰኞ እስከ አርብ፤ ደውሉ።